የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

# ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ ጥሪ

## በምዕራብ አውስትራሊያ ለሚትኖሩ ኢትዮጵያውያኖች በሙሉ፤

አምባገነኑ የአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ጭቆናና ግፍ እየተባበሰ መምጣቱ ግልፅ ነው። በተለይም በምርጫ 97 የኢትዮጵያ ህዝብ አንቅረው እንደተፋው የተረዳው የወያኔ-ኢህአዴግ መንግሥት ተቃዎሚዎችን ማሳደድና ህዝቡን መበቀል ግንባር-ቀደም ተግባሩ በማድረግ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍ ከምን ጊዜውም የከፋ ነው። የሥልጣኑን ዕድሜ ለማራዘም እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ በምርጫ ስም ለመነገድ ዝግጅቱን ከጀመረም ሰንበት ብሏል። የሚቀጥለውን ምርጫ የተለየ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ወያኔ በአንድ በኩል መንግሥት በሌላ በኩል ተቃዎሚ መስሎ በመቅረብ "በምርጫ አሸንፈናል" በማለት የጭቆና ሥርዓቱን ዕድሜ ለማራዘም የጀመረው ልዩ ዝግጅት ነው። ለመሠረታዊ ለውጥ የሚታገሉ ተቃሚዎች እንደይሳተፉ የተላያዩ መሰናክሎችን አዘጋጅቶ የስርዓቱ ታማኝ "ተቃዋሚዎችን" ይዞ ለምርጫ ለመቅረብ ሽር ጉድ እያለ ነው። በአንፃሩ በአቋማቸው የፀኑና የህዝብ ወገንነታቸውን በርዥምና መራራ ትግል ያስመሰከሩ ተቃዋሚዎች ትግላቸውን ከምን ጊዜም በበለጠ አጠናክርው እየገፉ ናቸው። ለዴሞክራሲና ለህዝብ በላይነት የሚደረገውን ቀጣይ ትግል በሚመለከት ገላፃ ለማድረግና በምዕራብ አውስትራሊያ ከሚኖሩትን ኢትዮጵያውያኖች ጋር ውይይት ለማድረግ በኢህአፓ ከፍተኛ አመራር አባል የሚመራ ቡድን ፐርዝ ከተማን ይጎብኛል። ክቡራን እንግዶቻችን፤

1. አቶ ወንድሙ አለሙ ፤ የኢህአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል
2. አቶ አበራ አስናቂ ፤ የኢህአፓ አህጉራዊ አመራር ኮሚቴ አባል ናቸው

በዚህ ታላቅ ህዝባዊ ስበሰባ ተገኝተው ለዴሞክራሲያዊ ነፃነት በሚደረገው ቀጣይ ትግል ዙሪያ የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ የሚዳሰስና የትግሉን የወደፊት አቅጣጫ የሚያመላክት ገለፃ እንድሰሙና ቀጥሎም በሚደርገው ግልፅና ነፃ ውይይት በመሳተፍ የበኩልዎን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ የአክብርዎት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ቀን ፤ መስከረም 6 2009 እ.ኤ.አ (6 September 2009)

ሰዓት ፤ 1 ፒ ኤም (1 pm)

ቦታው ፤ **Altone Park Leisure Centre**
**332 Benara Rd, Beechboro WA 6063**

ትግላችን ይቀጥላል!

የኢትዮጵያ ህዝብ ያቸንፋል!

የኢህአፓ አህጉራዊ አመራር ኮሚቴ